# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

ቁጥር 70 መስከረም 7 2001 ዓ.ም


አንብበው
ያስነብቡ!
አባዝተው
ያሰራጩ!

ዓላማችን ወያኔን ከሥልጣን በማስወገድ እራሳችንን እና አገራችንን ነፃ ማውጣት፤ የሰው ልጆች ነፃነት የተከበረባት፤ ፍትህና እኩልነት የሰፈነባት ኢትዮጵያን መገንባት ነው።

## የወያኔ ባለስልጣናት የህክምና ወጪ በከፍተኛ ሁኔታ እየጨመረ መምጣቱ ታወቀ

በተለያዩ በሽታዎች እንደተጠቁ የሚነገርላቸው የወያኔ ባለስልጣናት፣ በውጭ አገሮች ባሉ የህክምና ተቋማት ለሚያደርጉት የህክምና ክትትል፣ አገሪቱ በርካታ ሚሊዮኖችን እያወጣች እንደምትገኝ አንድ ስማቸው እንዳይጠቀስ የፈለጉ የወያኔ ባለስልጣን ለግንቦት 7 ከላኩት መረጃ ለማወቅ ተችሎአል።

ባለስልጣኑ ሰሞኑን ለግንቦት 7 የመረጃ ክፍል በላኩት መልእክት ላይ እንደጠቀሱት፣ ከአምባገነኑና ዘረኛው መለስ ዜናዊ ጀምሮ ያሉ የወያኔ ባለስልጣነት ለህክምና በተደጋጋሚ ወደ ውጭ አገራት በመመላለስ፣ የአገሪቱን ሀብት እየዘረፉ ነው።

የጠቅላይ ሚኒስቴር ጽ/ቤት ሃላፊና የካቢኔ ጉዳዮች ሚኒስትር በሆነው በብርሀኑ አዴሎ ፊርማ ለገንዘብና የኢኮኖሚ ሚኒስትር በጥር 1፣ 2000 በቁጥር ጠ80-አጠ27/02/12 የተጻፈውን ደብዳቤ ለዋቢነት አያይዘው የላኩልን ባለስጣኑ፣የአገሪቱ ፕረዝደንት፤ ጠቅላይ ሚንስትር፤ ምክትል ጠቅላይ ሚንስትር፤ የሁሉም ፈደራል ፕረዝደንቶችና ምክትሎቻቸው፤ በምንስቴሪነት ማዕረግ የተሾሙት ሚንስትሮችና ምክትሎቻቸው፤ የብሄራዊ ባንክ ገዥና ምክትሉን ጨምሮ ኮሚሽነሮች እስከነ ባሌበቶቻቸውና ልጆቻቸው ሳይቀሩ የውጭ አገር የህክምና ወጪያቸው የሚሸፈነው በመንግሰት መሆኑን ጠቅሰዋል።

በአሁኑ ሰአት ኢትዮጵያ 11 ሚኒሰቴሮች፣ 3 ኮርፖሬሽኖች፣ 6 ኤጀንሲዎች፣ ከ20 በላይ ኢንተርፕራይዞች፣ አውቶሪቲዎችና ቦርዶች፣ 11 ክልሎች፣ አንድ ጠቅላይ ሚኒሰትር፣ አንድ ም/ል ጠቅላይ ሚኒሰትር፣ አንድ ፕሬዚዳንት ያሏት ሲሆን፣ በነጻ ህክምናው ውስጥ የተጠቃለሉት ባለስልጣናት ቁጥር ልጆቻቸውን ጨምሮ ከ 300 እንደማያንስ መረጃው ያመለክታሉ።

ይህ ሁሉ ባለስልጣን ቢያንስ በአመት አንድ ጊዜ በውጭ አገር ሄዶ እንደሚታከም የታወቀ ሲሆን፣ ለአንድ ጊዜ ህክምናም መጓጓዣ፣ ሆቴልና ሌሎችንም ወጪዎች ጨምሮ ከ10 ሺ ዶላር በላይ ነው። **ወደ ገጽ 2 ዞሯል**


የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት
THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
OFFICE OF THE PRIME MINISTER

ቀን 01 ጥር 2000
Date
ቁጥር ጠ80-አጠ27/02/12
Ref. No.

ለገንዘብና የኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር
አዲስ አበባ

የኢፌዴሪ ፕሬዚዳንት፣ ጠቅላይ ሚኒስትር፣ ም/ጠቅላይ ሚኒስትር፣ ባለቤቶቻቸው እና 18 ዓመት ያልሞላቸው ልጆቻቸው የሕክምና ወጪ አሸፋፈን እንዲሁም የኢፌዴሪ የከፍተኛ የመንግሥት ኃላፊዎች ደመወዝና ጥቅማጥቅሞች ለመወሰን የወጣውን የሚኒስትሮች ምክር ቤት መመሪያ በተለይም የሕክምና ወጪ አሸፋፈንን በሚመለከት ማሻሻያ ያስፈለጋቸውን ነጥቦች በመመልከት እንዲሻሻሉ ተደርገዋል።

በመሆኑም የተሻሻለውን መመሪያ በሥራ ላይ እንድታውሉ የተወሰነ መሆኑን እናስታውቃለን።

ከሠላምታ ጋር
ብርሃኑ አዴሎ
የጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት ኃላፊ
የካቢኔ ጉዳዮች ሚኒስትር

ስልክ 011-1-22-67-57 Tel | ፋክስ 22 62 92 Fax | ፖ.ሣ.ቁ. 1266 P.O.Box | አዲስ አበባ ኢትዮጵያ Addis Ababa - Ethiopia

## ዘረኛው መለስ ዜናዊ የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የተፈጥሮ መዛባትን አስመልክቶ በሚያደርገው ስብሰባ ላይ አፍሪካን ወክሎ እንደሚሳተፍ ተገለጸ

የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ከጊዜ ወደጊዜ ትኩረት እየሳበ በመጣው የተፈጥሮ መዛባት ምክንያት አለም አቀፍ መፍትሄ ለመሻት እንደፈረንጆች አቆጣጠር በመጪው ዲሰምቤር በዴንማርክ ዋና ከተማ በኮፔን ሃገን በጠራው ስብሰባ ላይ አፍሪካን ወክሎ እንዲገኝ በቅርቡ በሊቢያ ዋና ከተማ በቲሪፖሊ ተደርጎ በነበረው የአፍሪካ ህብረት የመሪዎች ጉባዔ የተወከለው ዘረኛው መለስ ዜናዊ በዚህ ሳምንት መጨረሻ ወደኒዎርክ ለመንቀሳቀስ በዝግጅት ላይ መሆኑን ከውስጥ አዋቂ ምንጮች የተገኘው መረጃ አጋለጠ።

የወያኔ ቁንጮዎች በመከላኪያ ሰራዊት ውስጥ በነበሩት ከፍተኛ ወታደራዊ መኮንኖች ተባባሪነት አንዴ “የመፈንቅለ መንግሥት ሙከራ” ሳይውል ሳያድር ደግሞ “ባለስልጣኖችን የመግደል ሙከራ ተቀነባብሮብን ነበር” በማለት ካወጁ ወዲህ እንቅስቃሴያቸውን በከፍተኛ ምስጥር ለመጠበቅ መገደዳቸውን ያመለከተው የመረጃ ምንጫችን፡ በቅርቡ መለስ ዜናዊ ወደ ቤልጅየም ለህክምና ሂዶ በነበረበት ወቅት በቤተመንግሥት ውስጥ የኢሃደግ ስራ አስፈጻሚ ስብሰባ እየመራ እንደነበር ተደርጎ በመገናኛ ብዙሃን መገለጹ ምን ያህል የደህንነት ስጋት ውስጥ እንደወደቁ ያመለክታል ተብሎአል። የአሁኑም የመለስ ዜናዊ ወደ ኒዎርክ ጉዞ አስከመጨረሻው ሰዓት በሚስጥር እንደሚጠበቅና ከአገር መውጣቱ እንዳይታወቅም እንደተለመደው ከተማው ረጭ በሚልበት እኩለ ሌሊት ላይ በቻርተር አውሮጵላን ከአገር እንደሚወጣ ይጠበቃል።

እንደ መረጃ ምንጮች ገለጻ ኒዎርክ የሚገኘው የተባበሩት መንግሥታት ዋና መ/ቤት በኮፔን ሃግን ሊደረግ ለታሰበው ለዚህ ስብሰባ ቅድመ ዝግጅት ለማድረግ ከተለያዩ አህጉር ተወካዮች ጋር በሚቀጥለው ማክሰኞ ሴፕተምበር 22 ስብሰባ ይቀመጣል ። የመለስ ዜናዊም በዚህ ስብሰባ ላይ መጋበዝ በወቅቱ የኔፓድ ሊቀመንበርነቱና የተፈጥሮ መዛባት ላይ ለመምከር በተጠራው ስብስባ አፍሪካን ለመወከል በተሰጠው አዲስ ሹመት ምክንያት እንደሆነ ታውቆአል።
ከዋይት ሃውስ አካባቢ በተገኘ ሌላ መረጃ አዲሱ የአሜሪካ ፕረዝደንት ባራክ አባማ በዚህ ስብሰባ ላይ ለመሳተፍ ከሳብ ሰሃራን አፍሪካ አገሮች ከሚመጡ መሪዎች ጋር በዋይት ሃውስ ተገናኝተው ለመነጋገር ዕቅድ መያዛቸው ሲታወቅ ዘረኛውና አምባገነኑ መለስ ዜናዊ ከተጋባዦቹ እንግዶች አንዱ ሊሆን እንደሚችል ይጠበቃል ተብሎአል።

**ወደ ገጽ 2 ዞሯል**

## የዘረኛው መለስ ዜናዊ አገዛዝ መወገድ ያለበት መሆኑን አለም እየተረዳ መምጣቱ ተገለጸ

በኢትዮጵያ ውስጥ እየተፈጸመ ያለውን የሰብአዊ መብቶች ጥሰት ለማጋለጥና የኦባማ አስተዳደር ለዘረኛው መለስ ዜናዊ አገዛዝ የሚሰጠውን ድጋፍ በመቃወም ከትናንት በስቲያ በዋሽንግተን ዲሲ በተደረገው ሰላማዊ ሰልፍ ላይ የጄኖሳይድ ወች ፕሬዚዳንት ዶ/ር ግሪጎሪ ስታንተን ንግግር ባደረጉበት ወቅት እንደገለጹት፣ የመለስ አገዛዝ በህዝቡ ላይ እየፈጸመ ያለውን ሽብር የተለያዩ አለማቀፍ ድርጅቶች ትኩረት ሰጥተው እየተከታተሉት ነው ብለዋል። የመለስ አገዛዝ በጋምቤላ፣ በአማራ፣ በኦጋዴን፣ በሶማሊያና በሌሎችም አካባቢዎች በሚፈጽመው የዘር ፍጅትና የሰብአዊ መብት ጥሰቶች ምክንያት አገዛዙ መወገድ ያለበት መሆኑን ተረድተናል ያሉት ዶ/ር ስታንተን፣ የኦባማ አስተዳዳርም ለጉዳዩ ትኩረት መስጠት እንዳለበት አሳስበዋል።

ዶ/ር ካሳ አርጋው ለአሜሪካ ድምጽ ሬዲዮ ሲናገሩ፣ “የመለስ ዜናዊ አገዛዝ የኢትዮጵያን ህዝብ የማይወክል፣ ከደርግ መንግሰትም ያልተሻለ አገዛዝ ነው” ብለዋል።

በሺህ የሚቆጠር ህዝብ በተገኘበት ሰላማዊ ሰልፍ ላይ የተለያዩ ኢትዮጵያውያን በመለስ ዜናዊ አገዛዝ ላይ ያላቸውን ተቃውሞ እጅግ በሚማርክ ንግግር አሰምተዋል። አብዛኛው ተናጋሪዎች በውጭ የሚገኙ ኢትዮጵያውያን በጥቃቅን ነገሮች መለያየታቸውን አቁመው ለአገራቸው በአንድነት እንዲቆሙ የጠየቁ ሲሆን፣ ከአሁን በፊት ታይቶ በማይታወቅ ሁኔታም ከሁሉም ብሄሮች የተውጣጡ ኢትዮጵያውያን መሳተፋቸው ታውቋል።

## በመለስ ሎሌዎች ቂልነት እንስቃለን፤ ትኩረታችን ግን በወቅቱ ጥሪ ላይ ነው

ባሮች ሁሉ ነፃነትን ናፋቂ አይደሉም። ነፃነትን ለመናፈቅ “እኔ ነፃነት የሚገባኝ ሰው ነኝ” የማለት ብቃት ይጠይቃል። ባርነት የአስተሳሰብ አድማሳቸውን ያጠበባቸው ባሮች በነፃነት ውስጥ ራሳቸውን ማየት ስለሚከበዳቸው የለመዱት ባርነት እንዲቀጥል የተቻላቸውን ሁሉ ያደርጋሉ፤ ራሳቸውን በማዋረድ ለጌታቸው ያላቸውን ታማኝነት ይገልፃሉ።

ሰሞኑን በአገራችን የታዘብነው የዚህ ተመሳሳይ ነው። ባለታሪኮቹ ሁለት ቡድኖች ናቸው። አንደኛው መለስና ወያኔ ጓደኞቹን የያዘ የጌቶቹ ቡድን ሲሆን ሌላኛው ደግሞ እንደነ ተሾመ ቶጋ፣ ሺፈራው ሽጉጤ፣ አባዱላ ገመዳ፣ ኩማ ደመቅሳ፣ ሙክታር ከዲር፣ ተፈራ ዋልዋ፣ አያሌው ጎበዜ እና ደመቀ መኮንን ያለውን የያዘው የታማኝ ሎሌዎች ቡድን ነው። የጌቶቹ ቡድን ለሁለት ተከፍለው አጭር ድራማ ለመተወን ወሰኑ። መለስ “ስልጣኝ በቃኝ፤ አሰናብቱኝ” ሲል ሌሎቹ “የለም፤ በጣም አስፈላጊ ሰው ስለሆንክ መቆየት አለብህ” ሲሉ በመከራከር የየድርሻቸውን ገቢር ተወኑ። ድራማው የተዘጋጀው ለውጭው ተመልካች ነበር። አሳዛኝም አስቂኝም የሆነው ግን የሎሌዎቹ ቡድን መደናበር አጭሩን ድራማ ከታሰበው በላይ እንዲረዝም ማድረጉ ነው። ምስኪኖቹ ሎሌዎች ድራማው የእውነት መስሎዓቸው ደነገጡ፤ ሰማይ የተደፋባቸው መሰላቸው። መለስን “እባክህን ቆይልን፤ እባክህን ጋልበን” ሲሉ ተማፀኑት። “መልቀቅ ግድ ከሆነ እኛ እንልቀቅና አንተ ቆይልን” ሲሉ ተለማመጡት፤ አንዳንዶችም አልቅሰው ለመኑት። በመጨረሻ ጌታቸው መለስ ተለመናቸውና ድራማው ተጠናቀቀ። “ዶሮን ሲያታሏት በመጫኛ ጣሏት” ይሏል ይህ ነው። የዘመኑ ከተሜ ወጣቶች “ቱሪስት ብላ” የሚሉትን ነገር ከአሁን በኋላ “ኩማ ደመቅሳን ወይም ተሾመ ቶጋን ብላ” በሚል መቀየራቸው የሚቀር አይመስልም። መለስ እንዲህ ልቦናቸው የተደፈነ በባርነት ለማደር የሚለማመጡት ሎሌዎችን አፍርቷል።

ወያኔ የቆመው በወታደሩና በስለላ ተቋማቱ ጭካኔ መሆኑ ይታወቃል። እነዚህን ተቋማትን ተሾመ፣ ጁነዲን፣ ግርማ፣ ኩማ ወይም ተፈራ እንዲመራቸው ነው መለስ የሚለቀው? እነዚህ ተቋማት በሰው እንጂ በህግና በሥርዓት ተመርተው አያውቁም። ገና ከሎሌነት ነፃ ያልወጡ ሰዎች እንደምን እነኚህን ተቋማት የማዘዝ አቅም ይኖራቸዋል? ተቋማቱ አናት ላይ ያሉት ቱባ ቱባ ወያኔዎችስ እሺ ብለው ሊታዘዙላቸው ኑሮአል? ወይስ መለስ በበረከት፣ በቴዎድሮስ ወይም በአርከበ ሊተካ? ይህ ቢሆን ኖሮ የጉልቻ ለውጥ ሳይሆን የጉልቻዎች ቦታ መቀያየር ነበር የሚሆነው:: ይህም ቢሆን የሚታሰብ አይደለም። ከቦታው በጉልበት የሚያስነሳው ካልመጣ መለስ በፈቃዱ ሥልጣኑን ይለቃል ብለን ፈጽሞ አናስብም። ቢቻለው ሲሞትም ልጁ ትተካው እንደሆነ እንጂ ከልቡ የሚያምነውና የሚወደው አንድም ወዳጅ እንደሌለው እናውቃለን።

በበደኖ፣ በአዋሳ፣ በሀረር፣ በጋምቤላ፣ በሸኮ መዠንገር፣ በጎንደር፣ በኦጋዴን፣ በአዲስ አበባ፣ በሶማሊያ፣ በባድሜ የፈሰሰው የኢትዮጵያውያን ደም ይጮሃል። በረሃብ፣ በበሽታ እየረገፈ ያለው ወገን ፍትህን እየተማፀነ ነው። በጠመንጃ የታፈነው ወገን ብሶት እንደታመቀ ነው:: መለስ ይኸን መች አጣውና ነው ስልጣኑን በራሱ ፈቃድ ለመልቀቅ የሚቀብጠው? ለመለስ ሎሌዎች ከልብ ብናዝንም ተምረው ይመለሱ ይሆናል በሚል ተስፋ እንደ ፍቅር እስከ መቃብሩ ጉዱ ካሣ ጊዜዓችንን አናባክንም:: ትኩረታችን በወቅቱ ጥሪ ላይ ነው።

ዓላማችን ወያኔን ከሥልጣን በማስወገድ እራሳችንን እና አገራችንን ነፃ ማውጣት፤ የሰው ልጆች ነፃነት የተከበረባት፤ ፍትህና እኩልነት የሰፈነባት ኢትዮጵያን መገንባት ነው። ለዚህ የተቀደሰ ዓላማ መሳካት እያንዳንዱ ዜጋ ምን ማድረግ እንደሚኖርበት የንቅናቄዓችን ሊቀመንበር በዘመን መለወጫ መልእክታቸው ግልጽ አድርገዋል። እሳቸው እንዳሉትም ከሃዘንና ከንፈር ከመምጠጥ ወጥተን እያንዳንዳችን በተግባር ትንሽም ብትሆን ጠጠር የምንወረውርበት ጊዜ ነው::

ውድ የኢትዮጵያ ህዝብ ሆይ! የቀረበልህን የትግል ጥሪ ተግባራዊ አድርግ።

1. በየአካባቢው የሚገኙ የነፃነት ታጋዮች የሚያደርጉትን በእንቅስቃሴያቸው ታያለህ፡፡ የምትችል ሁኔታህን ካመቻቸህ በኋላ ተቀላቀላቸው። የማትችል መረጃ በማቀበል፤ ቢጠማቸው ውሀ በማጠጣት፤ ቢርባቸው በማብላት፤ መደበቅ የሚፈልጉትን በመደበቅ ተባበራቸው፡፡
2. ከማናቸውም የወያኔና የተለጣፊዎች የፓርቲ የንግድ የዝርፊያ ድርጅቶች፤ ወይንም በግለሰብ ስም እያደርጉ ከሚዘርፉት ድርጅቶቻቸው፤ ወይንም ከታወቁት ከእነሱ አጋር ነጋዴዎች ጋር ምንም አይነት የንግድ ውልም ሆነ የምርት መጠቀም አታድርግ፡፡ የእነሱን ቢራና ለስላሳ ከምትጠጣ ለነፃነትህ ስትል ውሃ ጠጣ። እነሱ ያመረቱትን ከምትለብስ የተቀደደ ልብስ ልበስ፤ በነሱ ሲሚንቶ ከምትገነባ ግንባታውን ለጊዜው ተወው፡፡ ይህንን ለራስህ ከውስጥህ ቁረጥ፡፡ ሌላው እስኪያደርገው አትጠብቅ፡፡
3. የመንግስት ሠራተኛ የሆንከው በሥራህ ላይ ለግም፤ በቀን ሰርተህ የምትጨርሰውን ሥራ ለሣምንት አቆየው፡፡ በመሥሪያ ቤትህ የሚደረገውን ዘረፋ፣ ሚስጥር ወይንም ማናቸውም ይጠቅማል ብለህ የምታስበውን መረጃ አንተን በማያጋልጥ መልኩ ለነፃነት ታጋዮች አሳልፍ።
4. እያንዳንዱ ነፃነቱን የሚናፍቅ ዘረኛነት ያንገሸገሸው ኢትዮጵያዊ በከተማም ሆነ በገጠር በቅርብ ከሚያውቃቸውና ከሚያምናቸው ጓደኞቹ ወይንም ዘመዶቹ ጋር ብቻ በመሆን አምስት እራሱን ሆኖ ህዋስ ይፍጠር፡፡ ይህ ህዋስ ስለአገሩ ጉዳይ የልቡን የሚወያይበት፤ በነፃነት ታጋዮች መገናኛ ብዙሀን የሚሰማውን ዜና የሚወያይበት፤ የሚቀርቡ ተግባራዊ ጥሪዎችን ተከታትሎ ተግባራዊ የሚያደርግበትና በአካባቢው ተግባራዊ መሆናቸውን የሚከታተልበት፤ የአካባቢውን መረጃ ለነፃነት ሃይሎች የሚያቀብልበት እና በማኅበራዊ ኑሮው የዘረኛነትን ሰንኮፍ የሚነቅልበት ህዋስ ነው፡፡ እነዚህ ህዋሶች የእርስ በእስ መተማመንና መረዳዳት የመሳሰሉ ለዘለቄታውም የሚበጁን ጠቃሚ ማኅበራዊ እሴቶችን የምናዳብርባቸው መድረኮች ይሆናሉ፡፡
5. አምነህበት ሳይሆን ለኑሮ ብለህ ወያኔ/ኢሕአዴግን የተቀላቀልክ በተለይ አባል ካልሆንክ ሥራ አትሰራም ተብለህ በውዴታ-ግዴታ የገባህ፤ በግልህ ልብህ የሚፈልገውን በነፃነት የመኖር ጥም ለማርካት ከነፃነት ኃይሎች ጋር ብዙ ልትተባበር ትችላለህ፡፡ ከሌላውም የበለጠ የማታምንበት ድርጅት ውስጥ በማስገባት ያዋረዱት አንተን ነውና ውርደትህን በሆድህ ይዘህ፤ እልህህን እነሱን ለመገዝገዝ ተጠቀምበት፡፡ በመጀመሪያ በአካባቢህ የሚገኙ ዜጎችን አትበድል፡፡ አባል በመሆንህ የምታገኛቸውን ሚስጥሮች አሳልፍ፤ የነፃነት ኃይሎች አደጋ ላይ የወደቁ ሲመስልህ አስታውቃቸው፡ በአካባቢህ ከሚኖሩ ዜጎች ጋር የሰላምና የመተሳሰብ ኑሮ ኑር፡፡
6. የኢትዮጵያ ወታደር፣ ፖሊስ፣ ደህንነት ወይንም ማናቸውም ይህን ዘረኛ መንግሥት ተታለህም ሆነ ተገደህ የምታገለግል ኢትዮጵያዊ “ዘረኛነት በቃኝ” በል፡፡ ለነፃነት፤ ለእኩልነት፤ ለአገር ክብር በሚታገሉ ወገኖችህ ላይ በትርህን አታንሳ፡፡ ከኢትዮጵያ ድሃ ህዝብ ታክስ እየተከፈለህ ጥቂት ዘረኞችን በስልጣን ለማቆየት ብለህ ከወገንህ ጋር ዘላቂ ቂም ውስጥ አትግባ፡፡ ለፖለቲካ ችግሮቻችን ፖለቲካዊ መፍትሄ እንዳንፈልግ በትእቢት ሁሉንም ረግጠን እንገዛለን ብለው የሚመኩት አንተን ከወገንህ ጋር ደም በማቃባት ነውና “እምቢ!” በላቸው፡፡ የነፃነት ኃይሎችን፤ የእኩልነት ኃይሎችን እርዳ፣ ተቀላቀል! ለዘረኞች ስልጣን ብለህ አትሙት!

የሙያ ማኅበራት፣ የፆታ ድርጅቶች፣ የመጽሃፍት ክበባት፣ የወጣትና የተማሪዎች ማኅበራት፣ የሠራተኞች ማኅበራት የዘረኞች መሳሪያ የመሆንን ተንኮልና ድቀት ተሻግረው ለዜጎች መብት መከበር እንዲቆሙ ታገል።

## የወያኔ ባለስልጣናት የህክምና ወጪ . . . ከገጽ 1 የዞረ

እንደ መለስ፣ አዲሱ፣ በረከትና ግርማ ወልደ ጊዮርጊስ የመሳሰሉት ደግሞ በአመት ከ 5 ጊዜ በላይ በውጭ አገራት እየተመላለሱ እንደሚታከሙ የታወቀ ሲሆን፣ ለጠባቂዎቻቸው የሚወጣውን ወጪ ጨምሮ ለእያንዳንዳቸው በአንድ ጊዜ ብቻ እስከ 100 ሺ ዶላር እንደሚወጣ ታውቋል።

ከደረሰን መረጃ ለመረዳት እንደሚቻለው በአንድ አመት ውስጥ ለባለስልጣናቱ የሚወጣው የህክምና ወጪ በትንሹ ከ15 ሚሊዮን ዶላር እንደማያንስ ይታመናል።

የአንድ ኢትዮጵያዊ አማካኝ አመታዊ ገቢ ከ150 ዶላር በማይዘልበት አገር ውስጥ ይህን ያክል ገንዘብ ለወያኔ ባለስልጣነት ህክምና መጥፋቱ ብዙዎችን ያነጋገረ ጉዳይ ሆኗል።ሌሎች ጥቅማጥቅሞች ሲደመሩ ደግሞ አገሪቱ ምን ያክል በወያኔ የቀን ጅቦች እየተበላች መሆኑዋን ለመረዳት አያዳግትም ያሉን አንድ አስተያየት ሰጪ፣ ወያኔ በየጊዜው የሚከዱትን ባለስልጣነት በጥቅም ለመያዝ በሚያደርገው ጥረት የአገሪቱ ሀብት እየተዘረፈ የሚቀጥለው ትውልድ እንዲከፈለው ይደረጋል ብለዋል።

ወጣቱ ትውልድ ጥቂቶች ለሚዘርፉት ገንዘብ እዳ ከፋዩ ራሱ መሆኑን ተረድቶ ከአሁኑ አገዛዙን መቃወም እንዳለበት አስተያየት ሰጪዎች ተናግረዋል።

## ዘረኛው መለስ ዜናዊ የተባበሩት መንግስታት. . . ከገጽ 1 የዞረ

ባራክ አባማ የኢሊኖይስ ሴናተር በነበሩበት ወቅት መለስ ዜናዊ በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ በፈጸመው ግዲያና ሰቆቃ ምክንያት ኢትዮጵያ የአሜሪካ ዕርዳታ እንዳይሰጣት የሚጠይቅ ኤች አር 2003 የተባለውን ረቂቅ ደንብ  የፈረሙ ሰው ከመሆናቸውም በላይ፣ በቅርቡ ተደርጎ በነበረው የጂ 8 አገሮች ስብሰባ እና በጋና ግብኝታቸው ወቅት በሰብዓዊ መብት ጥሰታቸው ምክንያት ፊት ነስተዋቸው ከነበሩት አምባገነን የአፍሪካ መሪዎች መለስ ዜናዊ አንዱ እንደነበረ መዘገቡ ይታወሳል።

የአባማ አስተዳደር ይከተላል ተብሎ በሚነገርለት አዲስ የፖሊሲ አቅጣጫ ምክንያት ክፉኛ የተደናገጠው የወያኔ አገዛዝ ላልፉት 9 ወራት የአሜሪካንን መንግሥት በሰበብ አስባቡ እያብጠለጠለ አንደቆየ የሚመሰክሩት አንዳንድ ታዛቢዎች በዚህች አጋጣሚ ከባራክ አባማ ጋር ማዕድ ለመቋደስ እድል የሚያገኘው መለስ ዜናዊና አቸፍቻፊዎቹ በተለመደው የማደናገሪያ ቋንቋቸው የአሜሪካን መንግሥት ፊቱን መለሰልን፤ ይህም በአገራችን ሰላሰፈነው ሰላም ፣የኢኮኖሚ እድገትና መልካም አስተዳደር ነው የሚል የፈጠራ ዲስኩር አቀነባበረው እራሳቸውን በማሞኘት ሌላውንም በርካሽ ፕሮፖጋንዳቸው እንደሚያደናቁሩት ይጠበቃል ብለዋል።

በግንቦት 7 የፍትህ የነጻነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ የህዝብ ግንኙነትና ቅስቀሳ ዘርፍ በሳምንት አንዴ የሚዘጋጅ ድርጅታዊ ልሳን

የፖስታሳጥን ቁጥር ፡- POBox: 4916
2003EX Haarlem, The Netherlands

# በዘረኞች አፈናና ግዲያ ሳንንበረከክ እውነተኛ የህዝብ ተወካዮችን መምረጥ የምንችልበትን ሥርዓት በትግላችን እንገነባለን

ከዝግጅት ክፍላችን

ባለፉት 50 ዐመታት አገራችን ኢትዮጵያ በቅርፅ የሚለያዩ በይዘት ግን እጅግ ተመሳሳይ የሆኑ የ3 መንግስታትን የፓርላማ ምርጫ አስተናግዳለች። የረጂም ዘመን ታሪክ ባለቤት የሆነዉ የኢትዮጵያ ህዝብ በታሪክ ዘመኑ ሁሉ ከትክክለኛ የፖለቲካ ምርጫ ተገልሎ የኖረ ቢሆንም “ምርጫ” ለሚባለዉ ፅንሰ ሃሳብ ግን እንግዳ ሆኖ የኖረበት ዘመን ያለ አይመስለንም። የዕድር አመራር ምርጫ፤የዕቁብ ዳኛ ምርጫ፤ የአካባቢ ሽማግሌ ምርጫና ሌላም ሌላ ምርጫ በተለያዩ የአገሪቱ አካባቢዎች በየዕለቱ ይካሄዳል። ስለሆነም የኢትዮጵያ ህዝብ ሌላ ሁሉ ቢቀር “ምርጫ” ማለት ከቀረቡለት አማራጮች ዉስጥ እሱ ያሰኘዉን በነፃነት መምረጥ የሚችልበት ማህበራዊ ክስተት መሆኑን ጠንቅቆ ያዉቃል። ከዚህ በተጨማሪ በስፋቱ፤ በጥልቀቱና በአላማዉ ከላይ ከተጠቀሱት የምርጫ አይነቶች ቢለይም - የፖለቲካ ምርጫም ቢሆን ህዝብ ይመሩኛል ብሎ እምነት የጣለባቸዉን ሰዎች የሚመርጥበትን መንገድ የሚያመቻች የፖለቲካ ክስተት እንጂ እንደ መለስ ዜናዊ አይነቶቹ ፀረ-ህዘቦች አምስት ዐመት እየጠበቁ እራሳቸዉን የሚሾሙበት የዘረኞች ድግስ አለመሆኑን የኢትዮጵያ ህዝብ በሚገባ ይገነዘባል።

በ1970ዎቹ መጨረሻና በ1980ዎቹ መጀመሪያ ላይ የአምባገነኑ ኮ/ል መንግስቱ አገዛዝ ለእጩ ተወዳዳሪዎች አንበሳ፤ነበርና ዝሆን የሚል ስያሜ ሰጥቶ “ድርጅታዊ አሠራር” የሚሉትን የኮሚኒስቶች ሚስጢራዊ አሰራር በመጠቀም የሚፈልገዉን ዝሆን፤አንበሳና ነብር እያስመረጠ በህዝብ ላይ ቀልዷል።የደርግን ስርዐት የተካዉና የአምባገነኖች ዘመን አበቃ! የዲሞክራሲ ዘመን ተጀመረ! የሚል አዋጅ እያወጀ አራት ኪሎ የገባዉ የመለስ ዜናዊ አገዛዝ ደግሞ ተወዳዳሪ፤ዳኛና አሸናፊ እሱ ብቻ የሆነበትን ምርጫ በማዘጋጀት ተስፋ የተጣለበትን የዲሞክራሲ ብልጭታ ጭራሽ ከድጡ ወደ ማጡ እንዲገባ አድርጓል።

በደርግ ዘመን በነበረዉ ምርጫ መራጩ ህዝብ ወደ ምርጫ ጣቢያ ከመሄዱ በፊት ማን እንደሚመረጥ ያዉቅ ነበር።መለስ ዜናዊ ያካሄዳቸዉ ምርጫዎችም ቢሆን ባአብዛኛዉ ተወዳዳሪ ስላልነበረባቸዉ ዉጤታቸዉ ከምርጫዉ በፊት ይታወቅ ነበር።ተወዳዳሪ ፓርቲዎች በመጠኑም ቢሆን በነበሩበት በ1997ቱ ምርጫ ደግሞ መለስ ዜናዊ በምርጫ ሥልጣን የማይለቅ መሆኑን በተግበር አሳይቷል። የመለስ ዜናዊ አገዛዝ በመጪዉ አመት በሚደረገዉ ምርጫ ከገዢዉ ፓርቲና መለስ ዜናዊ እራሱ የነፍስ አባት ሆኖ ክርስትና ካነሳቸዉ ፓርቲዎች ዉጭ ሌላ እራሱን ችሎ የሚወዳደር ፓርቲ እንደማይኖር እስከዛሬ በወሰዳቸዉ እርምጃዎች በግልፅ አሳይቷል። ከአሁን በኋላ በቀረችዉ የ9 ወር ግዜ ዉስጥ ደግሞ በድፕሎማቶችና በዕርዳታ ለጋሽ አገሮች ግፊት አንዳንድ ምዕራባዉያንን ለግዜዉም ቢሆን ዝም የሚያሰኙ ለኢትዮጵያ ህዝብ ግን ምንም ዋስትና የማይሰጡ አንዳንድ ብልጭታዎች ሊታዩ ይችሉ ይሆናል፤ ሆኖም እነዚህ ዉጤታቸዉ ከወዲሁ ታዉቆ የተቀነባበሩ ብልጭታዎች መለስ ዜናዊ እያቦካ ሲጋግር ከከረመዉ ድቅድቅ ጨለማ ጋር ሲተያዩ “አባይን በጭልፋ” ናቸዉ።

የዛሬ 5 ዐመት ነፃ ምርጫ ብሎ ተወዳዳሪዎችን ከጋበዘ በኋላ የመሸነፉን ወሬ ሲሰማ የአዉሬነት ጠባዩ ተቀስቅሶበት መፈክር ባነገቡ ወጣት ሠላማዊ ሠልፈኞቸች ላይ የጎዳና ለጎዳና ተኩስ የከፈተዉ ፀረ-ህዝቡ መለስ ዜናዊ “የለመደች ጦጣ ሁል ግዜ ሽምጠጣ” እንዲሉ ዘንድሮም ምርጫ እያለ ህዝብን ማታለል ጀምሯል። መለስ ዜናዊና እንደ እጁ ላይ ስልክ የሚጠቀምበት በረከት ስምኦን የዘንድሮዉ ምርጫ ከምን ግዜዉም በበለጠ መልኩ ዲሞክራሲያዊ እንደሚሆን ታናግረዋል። ለእነዚህ ሁለት የተንኮል አጠንጣኞች ዲሞክራሲ ማለት ምን ማለት እንደሆነ በዉል ባንረዳም ከንግግራቸዉ እንደምንረዳዉ ግን የሚቀጥለዉን ምርጫ ዉጤት ካሁኑ ጠንቅቀዉ ያወቁ ይመስላል። ይህንን ደግሞ በ2000 ዓም ሚያዝያ ወር ባካሄዱት የአካባቢ ምርጫ በሚገባ አሳይተዉናል።በዓለም የምርጫ ታሪክ ዉስጥ ያቀረቡት ተወዳዳሪ ሁሉ አሸንፎላቸዉ ምርጫዉን መቶ በመቶ ያሸነፉ ፓርቲዎች ቢኖሩ በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ በተከታታይ እራሳቸዉን የጫኑት የደርግ ኢሠፓና የህወሀት ኢህአዴግ ፓርቲዎች ብቻ ናቸዉ።

ለመሆኑ ምርጫ ማለት ምን ማለት ነዉ? ገዢ ፓርቲዎች መልካም ሥራ እስከሰሩ ድረስ ለምን በዚያዉ አይቀጥሉም?

ቀላልና ግልፅ በሆነ አማርኛ “ምርጫ” ማለት ህዝብን የሚወክሉ ሰዎች በእርግጥም ህዝብን የሚወክሉ መሆናቸዉን በህጋዊ መንገድ የሚያረጋግጥና የፖለቲካዉ ሥርዐት ህግን ተከትሎ የሚራመድ ለመሆኑ ዋስትና የሚሰጥ የዲሞክራሲ ሂደት ነዉ። እንደዚህ ሲባል ግን ምርጫ ሁሉ ዲሞክራሲያዊ ነዉ ማለት አይደለም፤ እንዲያዉም ጠለቅ ብሎ ለተመለከተዉ የዲሞክራሲ ዋናዉ ምልክት የህዝብ ድምፅ መስጠት ሳይሆን ህዝብ የሰጠዉ ድምፅ በትክክል መቆጠሩ ላይ ነዉ።እንግዲህ የዲሞክራሲ ትልቁ ቁም ነገር ድምፅ አሰጣጡ ላይ ሳይሆን ድምፅ ቆጠራዉ ላይ ነዉ ማለት ነዉ። በነገራችን ላይ ወያኔ ህጋዊ “መንግስት” አይደለም ስንል ህዝብ በምርጫ አልመረጠዉም ወይም የህዝብን የምርጫ ወሳኔ ቀይሮ እራሱን በመሳሪያ ኃይል ሥልጣን ላይ ያስቀመጠ አገዛዝ ነዉ ማለታችን ነዉ።

ከላይ ከፍ ሲል እንደተመለከትነዉ ምርጫ የህዝብ ተወካዮችንና የፖለቲካዉን ሲስተም ህጋዊነት የሚያረጋግጥ የዴሞክራሲ ሂደት ነዉ ብለናል፤ እንግዲህ ይህ ህጋዊ ማረጋገጫ ተከታታይነት እንዲኖረዉ ምርጫም በተወሰነ የግዜ ገደብ ዉስጥ በተከታታይ መካሄድ አለበት ማለት ነዉ። በሌላ በኩል ደግሞ የፖለቲካ መሪዎች እንደማንኛዉም ሰዉ የራሳቸዉ የሆነ ፍላጎትና ግብ ስላላቸዉ ለዘለቄታዉ ሊታመኑ አይገባም። አንዳንድ ገዢ ፓርቲዎች በስልጣን ዘመናቸዉ ሁሉ በጣም የሚያስመሰግን ስራ ሊሰሩ ይችላሉ ሆኖም እነኝህን ፓርቲዎች በህገ መንግስቱ መሠረት ህዝብ ደጋግሞ ይመርጣቸዋል እንጂ ፓርቲዎቹ እራሳቸዉ መልካም ሥራ ሰርተናል ብለዉ የስልጣን ዘመናቸዉን መቀጠል ወይም ይህንን ማድረግ የሚያስችላቸዉን ህግ ማዉጣት የለባቸዉም። ፈረንጆች ሲቀልዱ በግልገፅ እንደሚናገሩት የፖለቲካ መሪዎችና ዳይፐር (Diaper) ተመሳሳይ ናቸዉና ሁለቱም ቶሎ ቶሎ መቀየር አለባቸዉ ይላሉ። እዉነታቸዉን ነዉ አገልግሎት እየሰጠ የማይቆሸሽ ነገር የለምና የፖለቲካ መሪዎችም ሲቆሽሹ የግድ መቀየር አለባቸዉ። ዛሬ ሊጠራ በማይችል መልኩ የቆሸሸና መታጠብ ብቻ ሳይሆን ተጠራርጎ መጥፋት ያለበት ፓርቲ ቢኖር ዘረኛዉ የህወሀት ፓርቲ ነዉ።

የምርጫ ግዜ ደረሰ ሲባል ህዝብ ዉሳኔ የሚሰጥበት ግዜ ደረሰ ማለት ነዉ። በምርጫ ወቅት ህዝብ ጥቅሜን አላስጠበቁልኝም፤ የገቡልኝን ቃል አልጠበቁም ወይም አገር የመምራት ብቃት የላቸዉም የሚላቸዉን የፖለቲካ ሰዎች ወይም ፓርቲዎች አስወግዶ በምትካቸዉ ሌላ የመምረጥ ሙሉ መብት አለዉ።ይህ የህዝብ መብት ደግሞ መሪዎችም ሆኑ እያንዳንዱ ዜጋ ሊጠብቀዉና ሊያከብረዉ የሚገባ መብት ነዉ። የኢትዮጵያ የመከላከያ ሠራዊትና የፀጥታ ኃይሎች ለህዝብ የቆሙና ለህዝብ የሚታዘዙ ህዝባዊ አካል መሆናቸዉ የሚያረጋገጠዉ ይህንን የህዝብ መብት የማያከብሩ ወይም የህዝብን ዉሳኔ በኃይል የሚቀይሩ ቡድኖችን ሴራ ሲበጣጥሱና የህዝብን ዉሳኔ ሲያስከብሩ ብቻ ነዉ። በግንቦት 1997ቱ ምርጫ የኢትዮጵያ ህዝብ ስነ ስርአት በተላበሰ መልኩ ከጧት እስከ ማታ ደከመኝ ሳይል በነቂስ ወጠቶ ድምፁን ሰጥቷል፤ ሆኖም የኢትዮጵያን ህዝብ ለሚቀጥሉት 5 ዐመታት ማን ይምራዉ የሚለዉ ትልቁ ዉሳኔ የተወሰነዉ ድምፁን በሰጠዉ በኢትዮጵያ ህዝብ ሳይሆን የህዝቡን ድምፅ በቆጠሩት የፀረ-ህዝቡ የመለስ ዜናዊ ታማኝ ካድሬዎች ነዉ። እነዚህ ከሆዳቸዉ ሌላ ምንም ነገር አሻግረዉ መመልከት የማይችሉ ደካማ ካድሬዎች የህዝብን ዉሳኔ የቀየሩት የምርጫ ጣቢያ ሰራተኞችንና ድምፄን አላስነካም ያለዉን ህዝብ በመደብደብ፤በማሰርና በመግደል ጭምር ነበር።

ለመሆኑ “የሰጠሁት ድምፅ በትክክል ይቆጠርልኝ” ብሎ ጥያቄ ያቀረበን ሠላማዊ ወጣት በመትረዬስ ያስጨፈጨፈዉ ግፈኛዉ መለስ ዜናዊ ዛሬ ምረጡኝ እያለ የሚወተዉተዉ ማንን ነዉ? ይጦረኛል ብላ በርበሬና ጨዉ እየሸጠች ያሳደገችዉን አንድ ልጇን በአግዓዚ ጥይት የተቀማች እናት ግንቦት በመጣ ቁጥር ትዝ የሚላት መከፈል ያለበት የልጇ ደም ዕዳ ነዉ እንጂ የልጇ ገዳዮች እራሳቸዉን በምርጫ ሲሾሙ ማጀብ አይደለም። ቤተሰቦቹን “ደህና ዋሉ” ብሎ ወደ ሥራዉ የሄደ አባወራ ከሥራዉ ሲመለስ የልጆቹ መርዶ ሲነገረዉ፤ወላጅ እናት የጥይት ድምፅ በሰማች ቁጥር ት/ቤት የላከችዉን ልጅ ፍለጋ በየሆስፒታሉ ስትሮጥና ባጠቃላይ የአገር አደባባይ በአገር ልጆች ደም ሲቀላ ትንቅንቅ እንጂ ድብልቅ፤ግልግል እንጂ ድልድል ፍጥጫ እንጂ ምርጫ ለማን ይበጃል?

በዚህ ሰሞን “የመለስ ዜናዊን የሥልጣን መልቀቂያ ጥያቄ ኢህአዴግ ተቀበለ” ተብሎ የተነገረዉን የተለመደ የወያኔ የቅጥፈት ዜና ሁላችንም ሰምተናል። በመሠረቱ “ኢህአዴግ” ጥያቄ ቀርቦለት ዉሳኔ መስጠት ቀርቶ በኢትዮጵያ ጉዳይ ላይ ጥየቄ መጠየቅ እንኳን የማይችል ‘ተናገር’ ሲባል- የሚናገር ‘ዝም በል’ ሲባል- ደግሞ እንደ ህፃን ልጅ አፉን በሁለት እጁ ይዞ የሚያጎነብስ የሹምባሾች ስብስብ ነዉ።ይህንን ስንል ግን ኢህአዴግ ዉስጥ ሆነዉ የወያኔን ዘረኝነት በጀግንነት የሚዋጉትን ኃይሎች ሳንዘነጋ ነዉ። ኢትዮጵያ ዉስጥ ፈላጭ ቆራጭ ሆነዉ እያንዳንዱን ዉሳኔ የሚወስኑት እንደ መለስ ዜናዊ፤ስዩም መስፍን፤ስብሐት ነጋ፤አባይ ፀሐዬና አዜብ መስፍን አይነቶቹ ዘረኞች እናት ፓርቲያቸውን ህወአትንና ኢህአዴግ ተብየውን የተለጣፊ ፓርቲዎችን ስብስብ እንደሚዘውሩ ማን ይስተዋል?

መሰብሰብ፤መወያየት፤ከቦታ ወደ ቦታ መዘዋወርና ባጠቃላይ ገዢዉ ፓርቲ ያለ ምንም ጥያቄ የሚያደርጋቸዉን ነገሮች ማድረግ የተከለከሉ ተቃዋሚዎች ባሉበት አገር ዉስጥ “ገዢዉ ፓርቲና ተቃዋሚዎች ተወያዩ” ብሎ መለፈፍ በራስ ላይ ከማፌዝ ተነጥሎ የሚታይ አይደለም። ዉይይት የለዉጥ ምንጭ ነዉና ገዢዉ ፓርቲና ተቃዋሚዎች ለዉጥን ለመቀበል ዝግጁ እስከሆኑ ድረስ ዉይይት ሁሉም ሰዉ የሚወደዉና የሚደግፈዉ ነገር ነዉ። ነገር ግን በተቃዋሚነት ብቻ ሳይሆን በዜግነታችን ጭምር ማድረግ የምንችለዉን ትንንሿን ነገር ሁሉ ለማድረግ ብቸኛዉ መንገድ ለዘረኞች መስገድና ለሆድ ማደር ከሆነ አመክኖ፤እዉነትና እዉቀት ጠፍተዋልና በዚህ ሁኔታ ዉስጥ የሚደረግ ዉይይት “እባካችሁ ግዙን” ብሎ ከመለመን ተለይቶ አይታይም።

የቆምንለት ህዝባዊ አላማ ግቡን የሚመታዉ እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ለምንና፤ለማን እንደቆመ አንዲሁም ማንን እንደሚታገል በዉል ሲረዳ ነዉ። የምንታገለዉ ዘረኝነትን ለማጥፋት ነዉ እንጂ በልቶ የጠገበን ዘረኛ በተራበ ዘረኛ ለመተካት አይደለም። ትግላችን ወደኋላ ከሚጎትተንና የአገራችንን አንድነት አደጋ ላይ ከጣለዉ ከወያኔ ስርዐት ጋር ነዉ እንጂ ከግለሰቦች ጋር አይደለም። ስለዚህ መለስ ዜናዊ ኖረም አልኖረ ሥልጣን ለቀቀም አልለቀቀ ዘረኝነትና የሰብዓዊ መብቶች ረገጣ ከኢትዮጵያ ምድር ተወግደዉ ነፃነት፤ እኩልነትና ሠላም እስካልነገሱ ድረስ ትግላችን ይቀጥላል። **ወደ ገጽ 4 ዞሯል**

## በዘረኞች አፈናና ግፏያ ሳንንበረከክ እውነተኛ የህዝብ . . .

ከገጽ 3 የዞረ (ሃይለ ሃሳብ)

የግንቦት 1997 ምርጫ ባለቀ በአመቱ መለስ ዜናዊ ለአንድ የዉጭ አገር ጋዜጠኛ በሰጠዉ ቃለ መጠይቅ ይህ የያዘዉ የሥልጣን ዘመን ሲያልቅ የጠ/ሚኒስተርነቱን ቦታ እንደሚለቅ ተናግሮ ነበር። ይህ ደግሞ-ደጋግሞ የኢትዮጵያን ህዝብ ዉሳኔ የጣሰ ግለሰብ ሁለት ዐመት ቆየና በሱ በኩል ሥልጣን እንደ በቃዉ ፓርቲዉ ከፈለገዉ ግን የፓርቲዉን ዉሳኔ እንደሚያከብር ተናገረ። ነገሩ - “የማይነጋ መስሏት” ነዉና ዛሬ ሁሉም ነገር አልፎ ሰዉዬዉ በራሱ አፍ እንደተረተዉ የወያኔ ነገር “ግመል ይሄዳል - ዉሻም ይጮሀል” ሆኗል።ችግሩ ዉሻዉም ግመሉም ተረት ተናጋሪዉ እራሱ ሆነና ወይ አልተኬደ ወይ አልተጮኸ እንዳዉ ወደኋላ መንተት ብቻ ሆነ።

ለመሆኑ መለስ ዜናዊ ይህንን በሌብነት የያዘዉንና ዘጠኝ ወር የቀረዉን የሥልጣን ዘመኑን ለመጨረሱ ምን ዋስትና ኖሮት ነዉ እስከ 2007 ዓም ድረስ የመሪነቱን ቦታ ይዞ እንዲቀጥል ተፈቀደለት ተብሎ የሚለፈፈዉ? ደግሞስ የ2002ቱ ምርጫ ከመካሄዱ ገና ከዘጠኝ ወር በፊት መለስ ዜናዊ እስከ 2007 ድረስ መሪ ሆኖ እንዲቀጥል ከአሁኑ ከወሰኑ ማንን ያታለሉ መስሎአቸው ነው ምርጫ ምርጫ እያሉ እራሳቸውን እንቅልፍ ነስተው አጀቢ ለመሆን የተዘጋጁትን እረፍት የሚነሱት? የኢትዮጵያ ህዝብ ሆይ ቀልድም ቢሆን የሚጥመዉ በወጉ ሲቀለድ ነዉና ይህንን የጋጠወጦች ቀልድ ችላ ብለህ እራስህን ከጥፋት አገርህን ከመበታተን አድን። ይህንን አዲስ ዐመት የዘረኛውን የወያኔ አገዛዝ የመጨረሻ ዘመን ለማድረግ ኢትዮጵያዊ ሁሉ በያለበት ዘብ ይቁም! የወያኔ ዘረኞች ያዘጋጁልንን ትልቅ ፈተና አልፈን አንድነቷ የተረጋገጠ ኢትዮጵያን ለሚቀጥለዉ ትዉልድ ለማስተላለፍ ያለን ብቸኛ አማራጭ ፈተናዉን በድፍረት መጋፈጥ ብቻ ነዉ!።

## የየመን ፖሊሶች ከ 100 በላይ ኢትዮጵያውያንን አሰሩ

በወያኔ አገዛዝ የሚደርስባቸውን ግፍ በመሸሽና ውጤት አልባ በሆነ የኢኮኖሚ ፖሊሲ የተፈጠረውን የስራ አጥነት ሁኔታ በመሸሽ አገራቸውን ጥለው የተሰደዱት ከ100 በላይ ኢትዮጵያውያን፣ በየመን አገር በሚገኙ እስርቤቶች ውስጥ ጠያቂ በማጣት ታጉረው እንደሚገኙ ምንጮቻችን ከስፍራው ተናግረዋል።

አብዛኞቹ ከኦሮሚያና ከአማራ ክልል የመጡ ስደተኞች መሆናቸውን የየመንን ባለስልጣናት ዋቢ አድርገው የተናገሩት ምንጮቻችን፣ በወያኔው ተላላኪ በዶ/ር ተውፊቅ አብዱላሂ የሚመራው በዬየመን የኢትዮጵያ ኢምባሲ ባለስልጣናት ወደ ስፍራው ሄደው እንዳልጎበኙዋቸው ታውቋል።

እስረኞቹ በረሀብና በውሀ ጥም እየተሰቃዩ እንደሚገኙ ምንጮቻችን የተናገሩ ሲሆን፣ የየመን ባለስልጣናትም ወደ አገራችሁ ልትመለሱ ትችላላችሁ እያሉ በማስፈራራት ላይ መሆናቸውን ለማወቅ ችለናል።

በተያያዘ ዜናም፣ ወያኔ ግንቦት 7 የሚባል ድርጅት በየመን የሚገኙ ኢትዮጵያውያንን እያደራጀ መንግስቴን ለመገልበጥ እየሰራ ነው ሲል ለየመን ባለስልጣናት አቤቱታ ማቅረቡን የውስጥ ምንጮቻችን የተረዱ ሲሆን፣ የየመን የደህንነት ሰራተኞችም አንዳንድ ተፈላጊ የሚላቸውን ስደተኞች አሳልፈው እንዲሰጧቸው ጠይቀዋል። የመንን እንደሌላ የኢትዮጵያ ግዛት የሚቆጥሩት የወያኔ ባለስልጣናት፣ በዚያች አገር እየተገኙ የሚፈልጉትን ሲያስገድሉ የሚፈልጉትን ደግሞ ወደ ኢትዮጵያ ታስሮ እንዲላክ ሲያደርጉ እንደነበር የሚታወስ ነው።

## አይ መስከረም!

ዓመት ቆጥረሽ፣ ቀጠሮ አክበረሽ መምጣትሽ
ምን ጥቅም አለው ምልልስሽ - ካላበሰረሽን እፎይታ
ምን ሊጠቅመኝ ሰላምታሽ - የባዶ አውደ አመት ጋጋታ
ቅሪብኝ መስከረም፣ ዳግም አትምጭብኝ - ይብቃ
እንቁጣጣሽ ካልሆነ ሰላምና እፎይታ።

አደይሽ ምን ሊረባኝ - በእሾህ በአምኬላ ተጋርዶብኝ
አበባሽ ጋሪጣ ሆኖብኝ - ልምላሜሽ ደርቆብኝ
ዓመት ቆጥረሽ በተመጪ ምን ሊገባኝ
እረ ዋዲያ ቅሪብኝ!

**ከሆነልሽ በቃ በይኝ**

ተውሳኩን በክረምት ጎርፍ ሸኝተሽ
ሸረኛውን ሚርተኛውን አሰናብተሽ
በጥባጭ አደፍራሹን ጠራርገሽ
ላይመለስ መከራዬን አስምለሽ
ትመጪ እንደሁ ነይልኝ፣ ሰላም ይዘሽ
በአበባና በቄጠማ በርግብ ታጅበሽ።

**እንጂ፣**

ለወግ ብቻ ብቅ አትበይ - በዚያው ቅሪ
አንችም እንደኔ አቀርቅሪ - በጣት በጥፍርሽ አፈር ጫሪ።

ከሆነልሽ አግዥኝ - እናሸቀንጠረው ተጋግዘን
መከረየዬን፣ መከረሽን - የገራ ሸክማችን
‘አይዞህ በርታ’ በይኝ።

**አለያማ፤**

ምን ዋጋ አለው?
ልጆችሽ በጥይት ባንነው
የኔ ነፍስና ስጋ በስጋት ተለያይተው
ወዳጅ ዘመድ፣ ጎረቤት ተሸማቀው
ዓመት ቆጥረሽ ብትመጪ ምናችን ነው፤
የ ‘አበባዬ ሆይ’ ዘማሬሽ ማን ለጥመው?

**አይመስከረም! አይ መስከረም፤**

አላየሽ ኑሯችንን - አልሰማሽ ጉዳችን፤
በወገን መሀል ባዳ - ስደተኛ ባገራችን
ያባረሯት ሚዳቆ መስለን
‘ዕንቁጣጣሽ እንኳን ደህና መጣሽ’ ብንልሽ
ምን ደስታ አለንና - ምን ሊረባልሽ?

ማገሩ ላልቶ ቤታችን - ግድግዳው ዘሞ ጎጇችን
አዳራሽ እልፍኝ የለን - ግርማአው ተገፎ ቀያችን
ጭር ብሏል መንበራችን - የሃዘን ድባብ ጋርዶን።

አዬ መስከረም፣ አዬ ጉድሽ
አውዳመት በባዶ ቤት ይደምቅ መስሎሽ
ቀጠሮ አክብረሽ መምጣትሽ
አይ ያንች ነገር ወግ ማጥበቅሽ።

አንችን ሳይጠብቅ ዘመኑ ተለውጦ
ዓባይ አንግሶ፣ ደሃ ውጦ
አገር ረግጦ፣ ስዕብና ደፍጥጦ፤

እንባ እረሮ እንጅ ሳቅ የለን
አውዳመቱን ከአዘቦቱ መቸ ለይተን
መውሊድ ይሁን ፋሲካ፣ ዕንቁጣጣሽን መቸ አሰብን።

**አይ መስከረም፤**

ይልቅ ቃል እንግባባ እንማማል
የአዲስ ዘመን ተስፋችንን ላማደስ- ሐዘናችንን ለማቅለል፤
ያዥኝ እንጂ፤ አምጭ እጅሽን
እንፋቀር አንለያይ አንድ እንሁን
ካጋራ ተውሳካችን እንድንድን።

ጥርሳችንን ነክሰን እንነሳ
ጋሻችን ይመከት፣ ጦራችንም ይብሳ
እንባችን እንዲደርቅ እንዲያከትም አበሳ
አውዳመት እንዲደምቅ አደይ እንዲፈካ

**እንጂማ፤**

ካቻምናን ቀብረሽ - አምናን ገድለሽ
ተስፋ ማብሰሩ ቀርቶ አደይሽ
ዘንድሮ ማጣሁ ብትይ፣ ማን ዞሮ ሊያይሽ
አይ መስከረም ታዘብኩሽ፤
‘አበባዬ ሆይ’ ብትይኝ - አበባዬ ረግፎ እያየሽ
ጥላ ርቆኝ አንጀቴ ታጥፎ - ጭንቀት ገድሎኝ

**ኤዲያ ተይኝ!**

‘እንቁጣጣሽ ባመት ባመቱ ያምጣሽ’ አልልም
ለባዶ ተስፋ አልጓጓም፤ አልጸልይም
ኃዘን የማይገፍ አውዳመት አላከብርም፡-

**ዳሩ ግን፤**

አትቀየሚኝ መስከረም
ቢበዛብኝ ነው ቅጣት መኮርኮም

ፅኃይሽ እስኪሞቀኝ ታግሻለሁ
አደይሽ እስኪያደምቀኝ ጠብቂያለሁ፤

ይልቅ እኔን ምሰይ፣ እናምፅ
አጥፊ አደፈርሾን እንገስጽ
በመላው ኢትይጵያ - ከገጽ -ገጽ፤

አብረን ፍትህ እንሻ፤
እኔ በቅቶኛል - አንችሳ?

እኮ በይ መስከረም፣ ችጭኝ ቃልሽን
ዳግም ለተመጭ ባዶ እጅሽን
ፀሀይ አበባሽ፣ ደምቆ ሲያደምቅ ማይልን።

ነገ ከዘንድሮ እንዲሻል
እንደ አምናና ካቻምናው ሞቶ እንዳይቀር
በልምላሜሽ ተመስሎ ሊመጀን
ተስፋሽ እንዲታደስ - ተስፋችን እንዲመለስ
እንጣጣር አብረን - ለአዲስ ዘመን ለአዲስ ጅንበር
ሳይሆን እንቁጣጣሽ በቃል ብቻ - በግንባር ጭምር እንዲከበር
ፍትህና ሠላም ይሰፈን - የመነካከስ አባዜ ይቅር
ስቃዩ ፍዳው - ባውዳመትሽ ይቀበር።

**እንጂማ ፤**

ልምላሜሽ ደርቆብኝ - አይዳሰስ አይሸተኝ
ስቃይ መከራ ጋርዶብኝ
አደይሽ ምን ሊረባኝ - ምን ሊጠቅመኝ።

ስሚኝ መስከረም፤
ቃል ለምድር፣ ቃል ለሰማይ
እጇን አጣምሬ ላልቀመጥ ባገሬ ላይ
በጥረቴ ፍትህ ሰላም ላይ
አምክኜ ላስቀር የመከፋፈልን ሾተላይ
ቆርጫለሁና ቃሌን ተቀበይኝ።

የአዲስ ጅማሮ የምስራች - የታሪክ ትዝታ ቅኝት
የወራት ቁንጮ - ዝክረ ትውፊት፤
መስከረም፣ የአዲስ አመት አሃዱ
የዘመን ቀመር - የተስፋ ክንዱ
ያገር የወገን የባህል ቀንዱ
ከእንግዳህ ይብቃሽ ፌዝና ቀልዱ።
አንች የወራት በኩር አድምጭኝ
የወጋኝን ጋሪጣ ንቀይልኝ
ፍትህና ሰላም ውለጅልኝ
በቃኝ ብያለሁ - በቃ በይኝ
የምስራች ይዘሽ ልትመጭልኝ ቃል ግቢልኝ።

**ከሰውባገሩ ሆለችሳ፤ ስቶክሆልም፡ ስዊድን**
**መስከረም 1 ቀን 2002**


# የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ

## የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።

በ17870 KHZ በ 16 ሜትር ባንድ እና በ18350 KHZ በ19


**ውድ አንባቢዎቻችን**

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታስቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዮን ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዣችንን እናቀርባለን g7radio@ginbot7.org